የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 49
ADDIS ABABA 18th April, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፭/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለዘላቂና አካታች የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለት ዕድገት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ………ገጽ ፲፩ሺ፪፻፬

## Content

Proclamation No. 1135/2019

Government of the Italian Republic Loan Agreement for financing Inclusive and Sustainable Development of Agricultural Value Chain Programme Ratification Proclamation...Page 11204

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፭/፪ሺ፲፩

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለዘላቂና አካታች የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለት ዕድገት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፴ ሚሊዮን ዩሮ (ሠላሳ ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

### PROCLAMATION No. 1135/2019

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ITALIAN REPUBLIC

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 30,000,000 EUR (thirty million Euro) for financing Inclusive and Sustainable Development of Agricultural Value Chain Programme, was signed in Addis Ababa on 22nd day of June 2018;

**WHERE AS**, the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 5th day of April, 2019.

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows **:**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለዘላቂና አካታች የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለት ዕድገት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፭/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴ ሚሊዮን ዩሮ (ሠላሳ ሚልዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲ ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Government of the Italian Republic Loan Agreement for financing Inclusive and Sustainable Development of Agricultural Value Chain Programme Ratification Proclamation No. 1135/2019".

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa on 22nd day of June 2018 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of equivalent to 30,000,000 Euro (thirty million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

Done at Addis Ababa, this 18th day of April 2019

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**